

# ስትራቴጂያዊ እቅድ

2025-2030

**ፍሪደም ፈንድ**

THE FREEDOM FUND

በመላው ኔፓል ያሉ የNational Harawa-Charawa Rights Forum አባላት በአገራዊ ደረጃ ስብሰባ ላይ ለመታደም ተሰብስበዋል። ©Filmatory Nepal/ The Freedom Fund

# መግቢያ





በ2024 እ.ኤ.አ፣ ዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም ያደረግነውን አስር ዓመታት የዘለቀ ትብብርን በመዘከር ከፊት ለፊታችን ያለውን ጉልህ የሆነ ስራ እውቅና በመስጠት በግንባር ቀደምትነት የሚሰሩ አጋሮቻችንን ወሳኝ ጥረቶች እያከበርን ሲሆን እንደገና ለማስጀመር እና ዳግም ለማሰብ ትክክለኛዉ ጊዜ እንደሆነ ይሰማናል። ባለፈዉ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ውስጥ፣ ፍሪደም ፈንድ በሚቀጥለው ደረጃችን ወዴት መሄድ እንዳለበት ሰራተኞችን፣ የቦርድ አባላቶችን፣ የተቀባይ አጋሮችን፣ የፊት ተሰላፊ መሪዎችን፣ በተግባር የተለማመዱ ባለሙያዎችን፣ ለጋሾችን እና እህት ድርጅቶችን ጠይቀናል።

ይህንን ሂደት ያጠናቀቅነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለአስከፊ ብዝበዛ እየተጋለጡ ነው የሚለውን እውነታ ተረድተን፣ በታደሰ ግልጽነት እና በከፍተኛ ምኞት ነው። እስካሁን ድረስ በተማርነው ላይ በመገንባት፣ የእኛ የ2025-2030 ስትራቴጂ በግንባር ቀደምትነት የሚሰሩ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በሚገባ ትኩረት የሰጠ አዲስ ተልዕኮ፣ የለውጥ ጽንሰ ሐሳብ፣ ለእውነተኛ ትብብር ያለንን ቁርጠኝነት የሚያደምቅ የዋና ዋና እሴቶች ላይ በተደረገ ማሻሻያ የተገነባ ነው።። ስትራቴጂዉ ለሚቀጥሉት ስድስት አመታት ደማቅ ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚያገኙ ነገሮችን፣ እንዴት ለውጡን እንደምንለካ እና አጋሮቻችንን በተሻለ ለመደገፍ የምናደርጋቸው ቁልፍ ለውጦች እና የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት ቅድሚያ መስጠትን ይዘረዝራል።



በመጨረሻም፣ ይህ ስትራቴጂ ውስጣዊ የመመሪያ ሰነድ ብቻ ሳይሆን ለፊት መስመር አጋሮቻችን እና ሰፋ ላለው የጸረ ባርነት ሴክተር የታደሰ ቁርጠኝነት ነው።



ፎቶዎች፣ ከላይ ወደታች፦ በFreedom Fund’s Brazil ሆትስፖት ፕሮግራም ውስጥ ወጣቶች እና ባለሙያዎች የተሳተፋበት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዝግጅት ©Natália Corrêa/The Freedom Fund፤ Flavian የFreedom Fund ፕሮጀክትን በMaisha Girls Safe House በ 2023 ተቀላቅሏል ከዚያ ጀምሮ በጸጉር ሳሎን ውስጥ ለመቀጠር ችሏል ©Melanie Hargreaves/The Freedom Fund፤ Domani የግሮሰሪ ሥራዋን ለማዘጋጀት ከFreedom Fund የማስጀመሪያ ገንዘብ በማግኘት በFreedom Fund አጋር ከሆኑት Janachetana Dalit Sangam በሚመቻቸው የቁጠባ ቡድን ውስጥ አካል ነች ©Eva Jew/The Freedom Fund፤ ለአሳ አጥማጆች የቀረበው የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና አጋር Stella Maris ©Overgrown productions/The Freedom Fund

# የምናውቀው ነገር

## ባርነት አሁንም አለ

ወደ 50 ሚሊየን የሚገመቱ ሰዎች ዘመናዊ ባርነት ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ይህም ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የተሳሰረ እና በኃይል የሚደረግ የጉልበት ስራ፣ የህፃናት የከፋ  የጉልበት ብዝበዛ ፣የንግድ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በኃይል የሚደረግ ጋብቻ እና የቤት ውስጥ ባርነትን ጨምሮ የተለያዩ ከፍተኛ የብዝበዛ ዓይነቶችን  ያካትታል። ከእነዚህ 50 ሚሊየን ከሚሆኑት ሰዎች አንድ ሶስተኛው በግል ሴክተር የአቅርቦት ሰንሰለቶች ውስጥ ይበዘበዛል። ወደ አንድ አራተኛ የሚሆኑት በፍሪደም ፈንድ በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የሚሰጣቸው አገራት ውስጥ ማለትም፣ በባንግላዴሽ፣ በብራዚል፣ በኢትዮጲያ፣ በኢንዶኔዥያ፣ በኬንያ፣ በማይናማር፣ በኔፓል እና በናይጄሪያ ይኖራሉ። ሴቶች፣ ህጻናት እና ስደተኛ ሰራተኞች በማይመጣጠን መልኩ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ዘመናዊ ባርነት በበርካታ እና በተደራረቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ቀውሶች የሚቀጣጠል መሰረታዊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው። ባርነቱ በበርካታ የአለም ክፍሎች ማደጉን የቀጠለ ሲሆን  የአለም አቀፍ ማህበረሰብ እስከ 2030 እ.ኤ.አ የዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም የተባበሩት መንግስታት  የዘላቂ ልማት ግቦች ላይ እንደተገለጸው ዘመናዊ ባርነትን በ2030 እ.ኤ.አ ለማስቆም በገባው ቃል በጣም ወደኋላ ቀርቷል።

## በግንባር ቀደምትነት የሚሰሩ ድርጅቶች ወሳኝ ሚናዎችን ይጫወታሉ

ስር የሰደዱ እና ፍትሐዊ ያልሆኑ ስርዓቶች በብቃት ሊፈርሱ የሚችሉት እነሱን በሚገባ በሚያውቋቸው በችግሩ በተጠቁ  ግለሰቦች እና እነሱ በሚመሯቸው እና የሚያምኗቸው ድርጅቶች አማካይነት ነዉ። የባርነትን ችግር ለመከላከል ግንባር ቀደም የሆኑ  ድርጅቶች በአካባቢያዊ አውድ ውስጥ በመመስረት፣ ለሚሰሯቸው ማህበረሰቦች ተጠያቂ በመሆን ለረጅም ጊዜ በቁርጠኝነት የሚሰሩ ናቸው፣ ነገር ግን በርካቶቹ በታሪክ እና ሆን ተብሎ በዘዴ ማግኘት ከሚገባቸው ሃብት በታች ተሰጥቷቸዋል ። እና ምንም እንኳን የኑሮ ተሞክሮ ያላቸው ግለሰቦች መሪነት ለማንኛውም ውጤታማ የማህበራዊ እንቅስቃሴ ወሳኝ ቢሆንም፣ ከዘመናዊ ባርነት በተረፉ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶች ጉልህ የሆነ አለመካተት እና የኢንቨስትመንት እጥረት ገጥሟቸዋል። ከፊት ተሰላፊ እና ከዘመናዊ ባርነት በተረፉ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶች ጋር በቆየው የአስርት አመታት አጋርነት ፣ በሚገባ የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግላቸው፣ ሲደገፉ እና ሲገናኙ ምን ሊደረግ እንደሚችል የሚያሳይ በቂ ማስረጃ/መረጃ አለን።

## አሁን ከሌላው ጊዜ ሁሉ በበለጠ፣በግንባር ቀደምትነት የሚገኙ የባርነት ተቃዋሚ  የ ድርጅቶች የእኛን ድጋፍ ይፈልጋሉ።

እንደ አለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት፣ “በግዳጅ ከሚደረግ ስራ በተግባር የሚደረግ ኢንቨስትመንት እንዳሁኑ ጊዜ በጣም አስቸኳይ ሆኖ በፍጹም አያውቅም።” በቅርብ ጊዜ የነበረው ሪፖርት እንደገመተው የግዳጅ ስራን የማስቆም የሚያስፈልገው ወጪ $212 ቢሊየን በላይ ሲሆን ወጪው በየጊዜው  እያደገ ሲሆን የበጎ አድራጊ እና የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ለብቻው በቂ አይደለም። ከፍተኛ ገቢ ባላቸው አገራት የሚገኙ ለጋሾች በዘመናዊው ባርነት ግንባር ላይ ላሉት ተደራሽ አይደሉም፣ ከባድ የገንዘብ ድጋፍ መስፈርቶች ብዙውን ጊዜ የድርጅቶችን ራስን በራስ የማስተዳደር እና ተፅእኖን ያዳክማሉ። ገንዘብ ነክ ያልሆነ ድጋፍ አጋዥ ሊሆን ቢችልም፣  በመጨረሻ ድርጅቶች ዋነኛ ፍላጎታቸው ተለዋዋጭ፣ የረጅም ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚሆን በግልጽ አስቀምጠዋል። ለእንቅስቃሴ ግንባታ ለማበረታታት ሆን ተብሎ የተሰጠ ቦታ ሳይኖር፣ ለለሀብት ግብዓቶች መወዳደር እና የእምነት እጦት የስርዓቶች ለውጥ የሚፈልገውን ትብብር ሊሸፍን ይችላል።

## ፍሪደም ፈንድ  በግንባር ቀደምትነት የሚገኙትን   የጸረ ባርነት ድርጅቶችን እና እንቅስቃሴዎችን በገንዘብ ለመደገፍ፣ ለመሰብሰብ እና ለመደገፍ በትክክለኛ ቦታ ላይ ይገኛል።

ዘመናዊ ባርነትን ለማስቀረት ግንባር ቀደም ጥረቶችን  ለመደገፍ ቁርጠኛ የሆነ የትብብር ፈንድ እንደመሆናችን መጠን፣ ፣ ወሳኝ የሆነ ክፍተትን እንሞላለን፡- ለአጋሮቻችን በዋነኝነት የማይደረስ የሆነውን የገንዘብ ድጋፍ በማሰባሰብ እና ስራቸውን የሚያሻሽል እና በስፋት የስርዓት ለውጥን የሚያበረታታ ወደተጠናከረ ኢንቨስትመንት እንለውጣለን። ውጤታማ እና በአካባቢ የሚመራ የጸረ ባርነት ጣልቃገብነቶችን መለየት እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ረገድ  ምን እንደሚሰራ (እና ምን እንደማይሰራ) ተምረናል። ትብብርን የማበረታታት፣ የተጎዱ ማህበረሰቦችን በፊት መስመር ማስቀመጥ እና ኃይለኛ እንቅስቃሴዎች እድገትን የሚያመጡ የትብብር መሰረተልማት ውስጥ በመደገፍ  ልዩ የትብብር ችሎታን ገንብተናል። በከፍተኛ ግልጽነት፣ ቁርጠኝነት እና ትኩረት ከየትኛውም ጊዜ በተለየ ወደ ቀጣዩ ምዕራፋችን እየተሸጋገርን ነው ።

# እሴቶቻችን

### ማክበር

በባርነት በቀጥታ የተጎዱትን ሰዎች እውቀትና አመራር እናከብራለን

ከእኛ በፊት የሄዱት እና ከጎናችን አብረውን የሰሩት እውቅና እንሰጣቸዋለን

በተግዳሮቶች ውስጥ እርስ በእርሳችን እንደጋገፋለን እና የስኬቶቻችንን እውቅና እንጋራለን

በገንዘባቸው እውነተኛ ለውጥ እንድናመጣ የሰጡንን እምነት በፍጹም አንረሳም።

### ልህቀት

በምናፈስሳቸው ገንዘቦች ከፍተኛውን ተጽእኖ ለማምጣት እንጥራለን

በደንብ የሚገኝ ማስረጃ ላይ በመመስረት በጣም ውጤታማ በሆኑ ጣልቃገብነቶች ውስጥ ኢንቨስት እናደርጋለን

ስህተቶቻችን ለመስማት እና ከስህተቶቻችን ለመማር ያለማቋረጥ  እንጥራለን

ለዝርዝር ትኩረት እንሰጣለን

### ብርታት

ባርነትን ለማቆም ግንባር ቀደም ሆነው ከሚታገሉት ጋር  በአብሮነት እንቆማለን

ስኬት ፈጣን ወይም ቀላል ሊሆን በማይችልበት ቦታዎች እና ጉዳዮች ላይ እንሰራለን

የተሰሉ ስጋቶችን ለመውሰድ አንፈራም

በግልጽ እና በቀጥታ እንናገራለን

### ትብብር

በሰፊው ለውጥን ለማሳካት ትብብር አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን

የማህበረሰቦች እና አጋሮች ቅድሚያ የሚሰጡ ነገሮች ላይ ምላሽ እንሰጣለን

ስልጣንን እና ሃብትን በማጋራት ትህትናን እንለማመዳለን

ቃል የገባነውን እንፈጽማለን እንዲሁምየምንችለውን ምርጥ አጋር ለመሆን እንጥራለን

# የለውጣችን ጽንሰ ሐሳብ

**ችግሩ**
ባርነት አሁንም አለ። 50 ሚሊየን የሚጠጉ ሰዎች ዛሬ ላይ በአለም ዙሪያ ዘመናዊ የባርነት ስር ናቸው።

**ተልዕኳችን**
በከፍተኛ ደረጃ ዘመናዊ ባርነት በሚታይባቸው አገራት እና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በተግባር የሚለካ ቅነሳን ለማምጣት በግንባር ቀደምት የሚሰሩ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ኢንቨስት እናደርጋለን።

ግንዛቤዎች
ተግባራት
ውጤቶች

## የሃብት ማሰባሰብ

- ግንዛቤዎች: ዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም እየሞከሩ ያሉ በግንባር ቀደምት የሚሰሩ ቡድኖች በከፍተኛ ደረጃ የግብዓት እጥረት አለባቸው እንዲሁም ለጋሾች አነርሱን ለማግኘት እና የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ይቸገራሉ።
- ተግባራት: ዘመናዊ ባርነትን የማስቆምበሚደረገው የጋራ ግብ ዙሪያ የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ለጋሾችን በጋራ እናቀርባለን እንዲሁም የፊት መስመር ጥረቶችን መደገፍ አስፈላጊነትን እናስተዋውቃለን።
- ውጤቶች: የጸረ ባርነት ዘርፍ የተሻለ ግብዓት የሚያገኝ ሲሆን ለጋሾች የሚሰጡት ገንዘብ ከፍተኛ ተጽዕኖ ለማምጣት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## ኃላፊነት የተሰጣቸው የአቅርቦት ሰንሰለቶች

- ግንዛቤዎች: የንግድ ድርጅቶች በአቅርቦት ሰንሰለታቸው ውስጥ በሠራተኞች ብዝበዛ ውስጥ የሚሳተፉትን ባህሪያቸውን ለመቀየር ድጎማ ሊደረግላቸው ይገባል።
- ተግባራት: ኃላፊነት የሚወስዱ የአቅርቦት ሰንሰለቶችን ለማስተዋወቅ እና ግንባር ቀደም ድርጅቶች መሪነት እንዲጫወቱ ለማብቃት ምርመራዎችን፣ ጥብቅናዎችን እና ሙግቶችን ለማገዝ የገንዘብ ድጋፍ እናደርጋለን
- ውጤቶች: ንግዶች የግዳጅ የጉልበት ስራን ከአቅርቦት ሰንሰለቶቻቸው ለማስወገድ ከማህበረሰቦች እና ከሰራተኞች ተገኘ መረጃ ላይ ተመስርተው ተዓማኒነት ያለው እርምጃ ይወስዳሉ።

## የፊት መስመር ሆትስፖቶች

- ግንዛቤዎች: የፊት መስመር ድርጅቶች በከፍተኛ ስርጭት ባለባቸው አገራት ውስጥ ትኩረት ከተነፈጋቸው ማህበረሰቦች ጋር በቅርበት በመስራት የዘመናዊ ባርነት ስርዓቶችን ለማወክ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡ ናቸው።
- ተግባራት: በዓለም ዙሪያ ባሉ ከፍተኛ ስርጭት ባለባቸው ሆትስፖቶች ውስጥ የቅርብ እና የተረፉ መሪዎችን ቅድሚያ በመስጠት የፊት ተሰላፊ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎችን የገንዘብ ድጋፍ እናደርጋለን፣ እንሰበስባለን እንዲሁም እንደግፋለን።
- ውጤቶች: የሲቪል ማህበረሰብ አደረጃጀቶች ዘመናዊ ባርነትን በትብብር እና በዘላቂነት ለመቀነስ እና ለመከላከል አቅም አላቸው።

## ምርምር እና የእውቀት ማጋራት

- ግንዛቤዎች: መረጃን እና የተገኙ ትምህርቶች በመለዋወጥ የውጤታማ ጣልቃገብነቶች እድገትን በማስቻል የበለጠ የገንዘብ ድጋፍ እንዲገኝ እና በአለም ዙሪያ የባርነት ችግር የበለጠ ለመቀነስ ይረዳል።
- ተግባራት: በእኛ ሆትስፖት ውስጥ ዘመናዊ ባርነት እና ስፋቱን እና ተፈጥሮውን ለማስቀረት የተግባር እርምጃ የሚወሰድበትን እውቀት እንገነባለን እንዲሁም እናጋራለን።
- ውጤቶች: በማስረጃ ላይ የተደገፉ፣ በአካባቢ የሚመሩ አቀራረቦችን በመከተል የጸረ ባርነት ድርጅቶች፣ ለጋሾች እና መንግስታት የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ።

## ራዕያችን

ከባርነት የነጻ የሆነ ዓለም

# እንዴት እየተለወጥን እንደሆነ

## ተልእኳችንን ለማሟላት እና እሴቶቻችንን ለማካተት፣ እኛ፦

### 1 እንደ መሪ ገንዘብ ለጋሽ፤ አጋሮችን እንደግፋለን እና እንዲመሩ ተጨማሪ ቦታ እንሰጣለን

የፈሪድም ፍንድ ዋነኛ አላማ የፊት መስመር የጸረ ባርነት ድርጅቶችን እና እንቅስቃሴዎችን በገንዘብ ለመደገፍ፣ ለመሰብሰብ እና ለመደገፍ በትክክለኛ ቦታ ማስቀመጥ ነው። ተሞክሯችን የሚያሳየው ምርጥ መፍትሔዎች የሚመጡት ለፈጠራ እና ለመላመድ ቦታ እና ሃብቶቻቸውን ከሚያቀርቡ የፊት ተሰላፊ አጋሮች እንደሚመጡ ነው። ተጨማሪ ሃብቶቻችንን ለአጋር ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ እናስተላልፋለን እና ፍሪደም ፈንድ ከተተገበሩ ወይም ከተመሩ ተነሳሽነቶች እንርቃለን። የተቀባይ አጋሮችን ፍላጎት በሚያሟላ አካሄድ ሃብቶችን፣ መመሪያን እና የራሳችንን ትምህርቶች ወይም ልምምዶች በግልጽ በማጋራት በስትራቴጂ እና በአፈጻጸም ውስጥ ራሳቸውን እንደቻሉ እናረጋግጣለን። ፍትሃዊነት እና የኃይል ማጋራትን ማዕከል ያደረጉ አዳዲስ የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ ዘዴዎችንም እንመረምራለን።

### 2 ከፍተኛ ስርጭት ባለባቸው አካባቢዎች  ውስጥ ሃብቶቻችንን ማዋሃድ እና መሰብሰብ።

ባለፈው አስር አመት ከእኛ የእንቅስቃሴ ሂደት ፕሮግራሞች ትምህርቶችንና ልምዶችን  በማካተት የእኛን የሆትስፖት ሞዴል አዘምነናል። ባለፈው አስር አመታት፣ እነዚህ ፕሮግራሞች ከእኛ የጂኦግራፊ ትኩረት ባደረጉ የሆትስፖት ፕሮግራሞች በመለየት ተንቀሳቅሰዋል። የፍሪደም ራይዚንግ (Freedom Rising) የመሪነት ፕሮግራምን ወደ ሆት ስፖቶቻችን በማዋቀር የፍሪደም ራይዚንግ (ከዚህ ቀደም በሆትስፖት እና በጎረቤት አገራት የሚንቀሳቀሱ) በእኛ የሆትስፖት አገራት ውስጥ ብቻ አሁን ላይ ይንቀሳቀሳሉ። ይህ የውህደት ሞዴል በእኛ የሆትስፖት አገራት ውስጥ ላሉ አጋሮች ሰፋ ያለ እና ጥልቅ የሆነ የድጋፍ ክልልን እንድናገኝ ያስችለናል።








ፎቶዎች፣ ከላይ ወደታች፦ በFreedom Fund አጋር Indonesia Ocean Justice Initiative እና በGovernment of Central Java province መካከል የመግባቢያ ስምምነት ሲፈረም ©Armin Hari/The Freedom Fund፤ ከመካከለኛው ምስራቅ ወደ ኢትዮጲያ የተመለሰች ስደተኛ በFreedom Fund አጋር ከሆነው Agar Ethiopia የምግብ ዝግጅት ኮርሷን ስትወስድ ©Genaye Eshetu/The Freedom Fund፤ Rajvati Mandal፣ የHarawa-Charawa Rights ፎረም ማዕከላዊ ሰብሳቢ የHarawa-Charawa ሰዎች ነጻ መውጣታቸውን የኔፓል መንግስት ሲያሳውቅ ለጋዜጠኞች እየተናገረ ©Niranjan Shrestha/The Freedom Fund



## 3 እርዳታ አሰጣጥን እና  ግብዓት ማሰባሰብን ላይ  ተለዋዋጭ የገንዘብ ድጋፍን ቅድሚያ መስጠት።

የረጅም ጊዜ ተለዋዋጭ የገንዘብ ድጋፍ ፈጠራን፣ ትብብርን እና ዘላቂነትን ለመደገፍ ወሳኝ እንደሆነ እውቅና እንሰጣለን። በተቻለ ሁሉ፣ የባለብዙ አመት፣ ተለዋዋጭ ስጦታዎችን እናደርጋለን እና አላስፈላጊ ገደቦችን እንዲሁም የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶችን እናስወግዳለን። የገንዘብ ድጋፋቸው ከፍተኛ ገደብ የሌላቸው ለጋሾች ጋር መስራት ላይ ቅድሚያ እንሰጣለን እንዲሁም የበለጠ ተለዋዋጭነትን ለመስጠት ሌሎች ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ እንሰራለን።

## 4 ተጨማሪ ዘላቂ የሆኑ እና ፍትሃዊነትን የተላበሱ ውስጣዊ ክንውኖችን መገንባት

አስፈላጊ ሲሆን፣ ፕሮግራሞችን በተሻለ ሁኔታ ለማቀናጀት እና ሀብቶችን በግንባር ቀደምነት ለሚሰሩ አጋር ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ወደመስጠት ለማሸጋገር ቡድኖቻችንን እንደገና እናደራጃለን። ሰራተኞቻችንን በተቻለ መጠን ከማህበረሰቦች እና ከአጋሮች ጋር ቅርብ እንዲሆኑ የማድረግ ስልታችንን እንቀጥላለን።

በKaramoja የዩጋንዳ ሆትስፖት የማስጀመሪያ ፕሮግራም ያ መክፈቻ ክንውን፣ በNapak እና Moroto ክልሎች የልጅ ብዝበዛን ለማስቆም ፕሮጀክቶችን በመጀመር ላይ ©Robert Ilukol/ ፈሪደም ፍንድ

# ወደየት እየሄድን ነው

## በቀጣ ስድስት አመታት ውስጥ፣ እኛ፡-

### 1 በዘመናዊ ባርነት የተጎዱ ማህበረሰቦች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ለመፍጠር የገንዘብ ድጋፍ እናደርጋለን።

ዛሬ ላይ ያሉ ማህበረሰቦችን ጥበቃ እና ነጻነት በመደገፍ በረጅም ጊዜ የባርነት ስርዓቶችን ከስር ነቅሎ ለማውጣት መስራት እንደሚቻል እናምናለን። የፊት ተሰላፊ አጋሮቻችን የማህበረሰቦቻቸውን ፍላጎቶች ይገነዘባሉ፣ ስለሆነም በሆትስፖቶቻችን በትኩረት በምንሰራባቸው አካባቢዎች ከትምህርትና ከሠራተኞች ማደራጀት ጀምሮ ገንዘብ ድጋፍ ማድረጋችንን በመቀጠል የተረፉትን ሰዎች ከባርነት እንዲወጡ እና ህይወታቸውን ዳግም እንዲገነቡ እንደግፋለን። እስከ 2030 እ.ኤ.አ መጨረሻ በአለም ዙሪያ ያሉትን 2.5 ሚሊየን ግለሰቦች ህይወት በቀጥታ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሆትስፖት አጋሮቻችንን ማለትም በባርነት ሁኔታዎች ውስጥ ያሉትን እና አደጋ ውስጥ የገቡትን እንደግፋለን። በስምንት አገራት ላይ በአሁኑ ሰዓት እየተንቀሳቀሱ በሚገኙ አስር የሆትስፖት ፕሮግራሞቻችን በተጨማሪ፣ በሚቀጥሉት ስድስት አመታት ውስጥ እስከ ሶስት ተጨማሪ ፕሮግራሞችን ለመክፈት አቅደናል።

### 2 የኃይል ለውጥ ለማድረግ የስርዓት ለውጥን እናበረታታለን።

የስብስብ ኃይል ዘመናዊ ባርነትን ለማስቀረት ቁልፍ እንደሆነ እናምናለን እና በትልቅ ስፋት ባላቸው የስርዓት ለውጥ ላይ እንዲሰሩ የተለያዩ አካባቢያዊ ተሳታፊዎችን በጋራ የሚያመጣ የማህበረሰቦች ልምምድ በኩል ትብብርን እናቀላጥፋለን። ከመንግስታት እና የንግድ ስራዎች ጋር አብረው የሚሰሩ እንዲሁም እንደ አየር ንብረት ለዉጥ እና የግዳጅ ፍልሰት የመሳሰሉ የሚገናኙ ቀውሶችን ጨምሮ የዘመናዊ ባርነት መሰረታዊ ምክንያቶችን ለመፍታት፣ ለሚደርሱ በደሎች ስልጣን ያላቸውን ተጠያቂ ለማድረግ እና ፖሊሲዎችን እና ማህበራዊ ስርዓቶችን ለመቀየር የፊት መስመር ተሰላፊ ድርጅቶችን እንደግፋለን። ኃላፊነት ባለበት የእኛ የአቅርቦት ሰንሰለቶች ተነሳሽነት አማካኝነት፣ ኮርፖሬሽኖች በአቅርቦት ሰንሰለቶቻቸው ውስጥ የግዳጅ ስራን ለማስወገድ እና በእነዚህ ጥረቶች ውስጥ የፊት ተሰላፊ ቡድኖች እንዲመሩ ለማስታጠቅ ምርመራዎች፣ ጥብቅና እና ስልታዊ ሙግቶች የገንዘብ ድጋፍ እናደርጋለን። በ 2030 መጨረሻ ላይ፣ በፍሪደም ፍንድየሚደገፉ አጋሮች 20 ሚሊዮን ሰዎች የጉልበት ብዝበዛን በተሻለ የመቋቋም አቅም ባላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ እንዲኖሩ ያስችላሉ እና ለዘመናዊ ባርነት ምላሾቻቸውን ለማጠናከር በመንግስት፣ በንግድ እና ማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ።

## 3 በተለይ ከጉዳት በተረፉ ግለሰቦች ፤በማህበረሰቦች  እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎችን ለማጠናከር ኢንቨስት እናደርጋለን።

በፕሮግራሞች ላይ ብቻ ሳይሆን በድርጅቶች ስነምህዳሮች ውስጥ ኢንቨስት እናደርጋለን። በተለዋዋጭ የገንዘብ ድጋፍ በኩል፣ የረጅም ጊዜ ግንኙነቶች እና አቅርቦቶች ማለትም የእኛ የድርጅታዊ አቅም ምዘና መሳሪያ አይነት የረጅም ጊዜ ግንኙነቶች እና አቅርቦቶች አይነት ጠንካራ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ግንባታን በስልት አስተዋጽኦ እናደርጋለን። በሆትስፖት አገራት ውስጥ በእኛ የሰርቫይቨር ሊደርሺፕ ፈንድ (Survivor Leadership Fund) በኩል ንቁ የሆነ ተሞክሮ ካለው መሪነት ጋር ቅድሚያ እንሰጣለን። በአለም አቀፍ ፎረሞች ውስጥ የፊት መስመር መሪዎችን እንዲሁ ከፍ በማድረግ ኃይላቸውን እና ግለ ማህደሮቻቸውን እንዲገነቡ እናስችላለን። እስከ 2030 እ.ኤ.አ መጨረሻ፣ 200 በተረፉ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶችን ጨምሮ ቢያንስ 500 የፊት ተሰላፊ አጋሮች ድርጅታዊ ልማትን እንደግፋለን።



## 4 በፀረ-ባርነት ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች የተሻሉ አሰራሮችን እና ልምዶችን እንዲከተሉ ተጽዕኖ እናደርጋለን።

በራሳችን ብቻ ዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም አንችልም፤ በመሆኑም ውጤታማ የሆኑ ነገሮች ማስረጃ ባለፋት አስርት ዓመታት ውስጥ እያደገ ቢመጣም፣ ውጤታማ እና በአካባቢው የሚመሩ ጣልቃ ገብነቶችን ለማሳደግ ገና ብዙ ስራ ይቀረናል። ከባለሙያዎች እና ከፊት ተሰላፊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ስለ ዘመናዊ ባርነት ተፈጥሮ እና ስፋት/መጠን የሚያሳዩ ምርምሮች ላይ ኢንቨስት እናደርጋለን፣ እንዲሁም ያገኘናቸውን ትምህርቶች ለዋና ዋና የፀረ-ባርነት ተዋናዮች እናካፍላለን። ሌሎች የፀረ-ባርነት ድርጅቶች የፕሮግራም አወጣጥ እና የምርምር ምርጥ ልምዶችን እንዲወስዱ በግንኙነት እና በመሰብሰብ እንዲሁም የአጋሮቻችንን ስራ በማጉላት በንቃት አስተዋፅኦ እናደርጋለን።

## 5 ለተቀባዮች እና  ለጋሾች ሃብቶችን/ግብዓቶችን በማሰባሰብ ለጋሽ አጋር  በመሆን እናገለግላለን።

በመጨረሻም ብዝበዛ የኃይል አለመጣጣም እንደሆነ እና የበጎ አድራጊ ደጋፊዎችን በግንባር ቀድምትነት አንድ የኃይል አይነትን እንደሚወክል እናውቃለን። በተቀናጀ የገንዘብ ድጋፍ፣ ዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም የጋራ ፍላጎት ያላቸው ለጋሾችን በጋራ እናመጣለን። በግንባር ቀድም የጸረ ባርነት ድርጅቶች ለበለጠ እና ለተሻለ ጥራት ያለው የገንዘብ ድጋፍ ጉዳዩን ለማስፈጸም ከለጋሽ ማህበረሰብ ከስራችን ምርጥ ተሞክሮዎች ምሳሌዎችን እንጋራለን። በተጨማሪም በብዝበዛ እና በሌሎች ዓለም አቀፍ ቀውሶች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን እናቀርባለን። እስከ 2030 እ.ኤ.አ መጨረሻ፣ በጠቅላላ የገንዘብ ድጋፍ ቁርጠኝነቶች ውስጥ $350 ሚሊየን እናንቀሳቅሳለን።

ፎቶ፡- Survivor Leadership Fund በኢንዶኔዢያ በመሰብሰብ ላይ ©Saldi Ali/ፍሪደም ፍንድ

# ማጠቃለያ

እኛ ዘመናዊ ባርነትን ለማስቆም ባለን ቁርጠኝነት ጽኑዎች ነን፣ እንዲሁም ራዕያችንን በሚጋሩ በዓለም ዙሪያ ካሉ ድርጅቶች እና ለጋሾች ጋር ለመተባበር ቁርጠኞች ነን። የእኛ ጉዳይ ብዙዎች ለመፍታት በጣም ትልቅ ወይም በጣም የተወሳሰበ አድርገው የሚቆጥሩት ችግር ቢሆንም፣ ያ እውነት እንዳልሆነ እናውቃለን። ምን በተግባር እንደሚሰራ የሚያሳይ ማስረጃ፣ ግልጽ የለውጥ ማንሻዎች እና የብዝበዛ ስርዓቶችን ለመበተን የተዘጋጁ ኃይለኛ የፊት መስመር እንቅስቃሴዎች አሉን።

በጋራ፣ ከባርነት የጸዳ አለም መገንባት እንችላለን።







ፎቶዎች፣ ከላይ ወደታች፦ የFreedom Fund አጋር የኮሚቴ አባላት SPAN Batulubang በIndonesia ©Armin Hari/The Freedom Fund፤ በState Palace በ Recife, Brazil, ሰልፍ ላይ ተሳታፊው የልጆች የንግድ ወሲባዊ ብዝበዛ ለማስቆም የስቴት መንግስት የሚያደርጋቸውን ጥረቶች እንዲጨምር ተሟጋች እየሆኑ፤ ©Natália Corrêa/The Freedom Fund፤ Ufim ሃብታቸውን በማሰባሰብ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት መሬት በሊዝ የያዙ ከHarawa-Charawa ማህበረሰብ ውስጥ የተውጣጣ የግብርና ቡድን አባል ነው ©Eva Jew/The Freedom Fund

# የባለድርሻ አካል ምክክር ሂደት ማጠቃለያ

### ማጠቃለያ ዳራ

ፍሪደም ፈንድ አይ.ጂ. አድቫይዘርዝ (I.G Advisors) የተባለውን ድርጅት ስትራቴጂያዊ የዕቅድ ዝግጅት ሂደት እንዲያመቻች ኃላፊነት ሰጥቶታል። I.G በሕዝብ፣ በግል እና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ዘርፎች መሃል ላይ የተቀመጠ፣ በማህበራዊ ተፅዕኖ መስክ ላይ ዓለም አቀፍ ትኩረት ያለው የስትራቴጂ አማካሪ ድርጅትየስትራቴጂ አማካሪ ድርጅት ነው። ከፍሪደም ፈንድ ከፍተኛ አመራር ቡድን እና ከሠራተኞች መሪ ኮሚቴ ጋር በመሆን I.G ለድርጅቱ የወደፊት መንገድ የሚገልጽ ጥብቅ፣ ሁሉን አሳታፊ እና አበረታች ሂደት በጋራ ቀርጾ አመቻችቷል።

## ሂደት

ሂደቱ በ2024 እ.ኤ.አ ቆይታ ውስጥ ሶስት ምዕራፎች የተከናወነ ነበር:-

- የመነሻ ምዕራፍ፤ ቁልፍ ባለድርሻ አካል ቡድኖች ያሳተፈ፣ በአሰራር መንገዶች እና  እቅዶች ላይ ማስጀመር
- የእውቀት መሰብሰቢያ እና ትንተና ምዕራፍ፤ ቁልፍ ከሆኑ የባለድርሻ ቡድኖች ጋር የጠበቀ ምክክር እና የምክክሩ ግኝቶችን የሚያጠቃልል የትንተና ሪፖርት በማጠናቀቅን፤ የእውቀት መሰብሰብ እና የትንታኔ ደረጃ።
- የስትራቴጂ ፈጠራ እና ንድፍ ምዕራፍ፤ ከፍሪደም ፍንድ የበላይ አመራር ቡድን  ጋር የንድፍ ወርክሾፖች ንድፍ፣ ድራፍቲንግ፣ ከቁልፍ የባለድርሻ ቡድኖች ጋር ሙከራ ማድረግ እና በቦርዱ ግምገማ እና ማጽደቅን የያዘ የስትራቴጂ አፈጣጠር እና የንድፍ ደረጃ።

## ባለድርሻ አካላት እና ምክክር  ዘዴዎች

በዚህ ሂደት ውስጥ የሚማከሩ ባለድርሻ አካላት ሰፊ የእይታዎች ስፋት፣ ተምክሮዎች እና ከፍሪደም ፍንድ ጋር ያሉ ግንኙነቶችን ይወክላሉ። በዳሰሳ ጥናቶች፣ በቃለመጠይቆች፣ በትኩረት ቡድኖች እና በዴስክ ምርምር በኩል፣ I.G. የጸረ ባርነት ሴክተር አሁናዊ ስነምህዳር እና የፍሪደም ፍንድ  ሚና እንዲሁም የድርጅቱ የለውት ጽንሰ ሃሳብ፣ ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች፣ ፕሮግራሞች እና ግቦች እንዲሁም የክንውን አንድምታዎችን ያዘሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን አስኗል።

በዚህ  የምክክር ሂደት ውስጥ ሁሉ  ለተሳተፋ ሰዎች እና ስትራቴጂያችንን እንድንገልጽ ለረዱን ሰዎች ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን። እነዚህ ቡድኖች እና ጥቅም ላይ የዋሉ ምክክሮች ዘዴዎች ከታች ተዘርዝረዋል፡-

| የባለድርሻ አካላት ቡድን | የማማከር ዘዴዎች |
|---|---|
| ሰራተኞች | ቃለ መጠይቆች፣ የዳሰሳ ጥናት፣ የትኩረት ቡድኖች፣ በአካል የሚደረጉ ወይይቶች |
| ቦርድ | ቃለመጠይቆች፣ የዳሰሳ ጥናት፣ የትኩረት ቡድን |
| የአቻ ድርጅቶች መሪዎች፣ ገንዘብ ለጋሾች እና ሌሎች ውጫዊ ባለድርሻ አካላት | ቃለመጠይቆች፣ የዴስክ ምርምር |
| ከአሁናዊ የፕሮግራም አካባቢዎች ያሉ የገንዘብ ተቀባይ አጋሮች | የዳሰሳ ጥናት፣ የትኩረት ቡድኖች |
| የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን(የሚከተለውን ይመልከቱ) | የትኩረት ቡድኖች |

በሁሉም ባለድርሻ አካላት ቡድኖች እና የምክክር ዘዴዎች የቋንቋ ተደራሽነት ዋነኛ ትኩረት ነበር። የአጋር ድርጅቶች  የዳሰሳ ጥናቶች ከአሥር በሚበልጡ ቋንቋዎች የተተረጎሙ ሲሆን የትኩረት ቡድኖች በአካባቢው ቋንቋዎች ወይም በአስተርጓሚዎች በኩል ተመቻችተዋል። ባለድርሻ አካላት በሚመቻቸው ሁኔታ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የቃልም ሆነ የጽሑፍ የመገናኛ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።

## የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን

ምንም እንኳን በዳሰሳ ጥናቶች እና የትኩረት ቡድኖች በኩል ማማከር የተሰጣቸው የፈሪደም ፈንድ አጋሮች የዘመናዊ ባርነት የተኖረ ልምድ ጋር በማህበረሰብ አባላት እና ግለሰቦች የሚመሩ በርካቶችን ቢያካትትም፣ የማህበረሰብ አማካሪ ቡድንን በመቅረጽ የበለጠ ታሳቢ የተደረገበት አቀራረብን ለመውሰድ ፈልገናል። የዚህ ቡድን ስድስት አባላት ሚና ዘመናዊ ባርነትን የመፍታት አውድ ውስጥ የእነርሱ እና የማህበረሰቦቻቸውን ቅድሚያ የሚያገኙ ነገሮች እይታን ለማቅረብ፣ በጸረ ባርነት ቦታ ውስጥ ከፈሪደም ፈንድ ሚና ጋር የተገናኙ ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ ሃሳብ አቅራቢ ሆኖ ለማገልገል እና አዲሱ የስትራቴጂ በዋናነት ማዕከል ያደረገው  በተረፉ ሰዎች እና ማህበረሰቦች በዘመናዊ ባርነት በጣም የተጎዱት ላይ ማዕከል እንዳደረገ ለማረጋገጥ ካለው የተወሰነ ስጋት ጋር በአቀራረቦች እና ሰነዶች ላይ ግብረመልስን ለማቅረብ ነው። በውስጣዊ የእጩነት ሂደት በኩል ቅጥርን በመከተል፣ በ2024 እ.ኤ.አቆይታ ባለው የሶስት ግማሽ ቀን ወርክሾፖች ውስጥ አባላት ተሳትፈዋል እንዲሁም ለሰጡት ጊዜ ማካካሻ አግኝተዋል።

የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን አባላት ላደረጉት አስተዋጽዖ ልዩ የሆነ ምስጋናን እናቀርባለን።

Ganesh Bahadur BK, Rastriya Dalit Network, Nepal

Jessica Nhkum, Kachin Women's Association Thailand (KWAT)

Iweng Karsiwen, KABAR BUMI, Indonesia

Maurine Ayodi, Baridi kwa Baridi Women CBO - Busia, Kenya

Rosana de França, Coletivo Mulher Vida, Brazil

Yenenesh Tilahun, KASMA Charity Organization, Ethiopia

# ራዕያችን

ከባርነት የነጻ የሆነ ዓለም

# ተልዕኳችን

በከፍተኛ ደረጃ ዘመናዊ ባርነት በሚታይባቸው አገራት እና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በተግባር የሚለካ ቅነሳን ለማምጣት በግንባር ቀደምት የሚሰሩ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ኢንቨስት እናደርጋለን።


**The Freedom Fund (UK)**
Lower Ground
Caledonia House
223 Pentonville Rd
London, N1 9NG
+44 20 3777 2200

**The Freedom Fund (US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org



The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).